# አዳም እና ያላለቀው አብዮት
**Teshale Kebede Bedriya**

“ያለፈውን ሳላስብ የዋልኩበት ጊዜ ስለሌለ በትክክል ዛሬን እየኖርኳት አይደለም ። ሁለመናዬ ገና ቁስል ነው" (መረቅ ፥310)

***

መቼም በአለም ታሪክ ውስጥ እንደ ዘመናዊነት አማላይና ማራኪ ነገር ያለ አይመስለኝ ። የተለያዩ ሃገሮች ዘመናዊነትን ለማዋለድ በብዙ ጥረዋል ፤ ለፍተዋል። አንዳንዶቹ ብልሃቱና እውቀቱ ሰምሮላቸው ያለሙትን የተመኙትን ሲያገኙ ሌሎች ደግሞ ጥረታቸው መና ቀርቷል ። ኢትጵያም የዝመና ፕሮጀክቱ ከከሸፈባቸው መካከል ታሪክ መዝግቧታል። የዚህ ፕሮጀክት አለመሳካት የኢትዮጵያ የታሪክ ደርዝ ውስብስብ በሆኑ ቀውሶች የተሰፋ እንዲሆንም አድርጎታል፡፡

ለመሆኑ ይህ ዘመናዊነት ምንድን ነው ?

ሚሼል ኸርድ እና አንቶኒዮ ኔግሪ ‘Empire’ በተሰኘው ድንቃይ ስራቸው ውስጥ እጅግ የሚገርም ሀሳብ ያስቀምጣሉ፤

ዘመናዊነት ወጥነት ያለው ፅንሰ ሃሳብ አይደለም፤ ከዚያ ይልቅ በሁለት በማይታረቁ ግዙፍ የተቃርኖ ሃሳቦች ውስጥ የሚገኝ ነው ይሉናል ። የመጀመሪያው ምድራዊ የሆነና ስር ነቀል ብሎም የህይወት ውቅርን የሚተልመው በተጨባጩ አለም ውስጥ ባለ አቀራረብ ነው ። ሁለተኛው አቀራረብ ሰማያዊ (ተምኔታዊ) ሲሆን ይህም ከተጨባጩ አለም በተቃራኒ የቆመ ነው ። በዚህም ዘመናዊነት ራሱ በቀውስ እና ግጭት መሰረት ላይ የተገነባ ፅንስ ሃሳብ ነው ይላሉ ...

“Modernity is not a unitary concept but rather appear in at least two modes:- The first mode is radical revolutionary process . This modernity declares the immanence of the new paradigm of the world life .The second mode of modernity poses a transcended constituted power against an immanence constituent power order against desire.

ተሻለ ጥበቡ (ፕ /ር) ፣(Modernity, Eurocentrism, and radical politics in Ethiopia, 1961–1991) በተሰኘው ጥናታቸው ኢትዮጵያ በሰላሳ ዓመት ውስጥ ሶስት ተደራራቢ አብዮቶችን አካሂዳለች ይሉናል ፣

“....three respective revolutions took place in Ethiopia: the Eritrean revolution that was begun in 1961 by the ELF and achieved its goal of Eritrean independence in 1991, and 1993); the Tigrayan revolution that began in 1975 with the formation of the TPLF and culminated in EPRDF’s Capture of power in 1991; and the 1974 all-Ethiopian revolution.

እነዚህም የኤርትራ የነፃነት ትግል ፣ የህዋሓት ስልጣን ላይ መውጣትና በመላው አገሪቱ የተካሄደው አብዮት በማለት ያትታሉ ። ከዚሁ ጥናታቸዉ ተጨማሪ ነጥብ ልዋስ ፤

“.... የኢትዮጵያ ማርክሲስቶች ጊዜያቸውን ያጠፉት በአብዮታዊ የድርጊት ዕቅድ ላይ በማተኮር እንጂ በማርክሳዊ ንድፈ ሐሳብ ማብራሪያ ላይ ወይም አውዳዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው በመስራት ላይ አልነበረም። "

ፓምፍሌቶችና ብሮሸሮች በማራባት ነበር የተጠመዱት ። ለምሳሌ አዲስ ሕይወት በተባለ የብዕር ስም የተፃፈ ባለ 115 ገጽ ብሮሽር አንዱ ነው ይላሉ ፕ/ር ተሻለ ጥበቡ ፣

" ...Ethiopia’s existence as a ‘modern State’ The same historical forces that created the ‘Gold Coast’, the Sudan and Kenya, were the very ones that created modern Ethiopia (1975 ፥1)

ይህንንም የዘመናዊት ኢትዮጵያን አፈጣጠር ‘ጎልድ ኮስት በአሁኑ አጠራር ጋና’ ፣ ሱዳንና ኬንያን በፈጠሩ ታሪካዊ ሃይሎች አማካኝነት ነው ኢትዮጲያም የተፈጠራችው ። ይህንን እውነታ መገንዘብ ዘመናዊቷን ኢትዮጵያ ከእነዚህ የአፍሪካ መንግስታት የበለጠ ጥንታዊነት እንደሌላት ለመገንዘብ ያስችላል ይላል።

***

የኢትዮጵያን አብዮት በፈጠራ ስራዎቹ በሚገባ በመፈተሽና የነበረውን ታሪካዊ ፣ማህበረሰባዊ ፣ ፖለቲካዊና ስነልቦናዊ ሁኔታዎችን በአግባቡ አንጥሮ በመፈከር ብሎም በመከየን አዳም ረታን የሚያህል ደራሲ ማግኘት ይከብዳል ።

ከደራሲው ድንቃይ ስራዎች መካከል አንዱ የሆነው ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ (የሰባት መንገዶች ወግ) የፈጠራ ስራ ውስጥ የጉዳያችን ማጠንጠኛ የሆነው ታሪክ እንጥለፍ ፤
” ...ከሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ወደ ሆድ ያባውን ንቃት ያወጣዋል የተሸጋገርኩት እዚህች መንገድ ጠርዝ ያለች አንዲት አልባሌ ሱቅ ጀርባ ለጥናት ክበብ ተጎዝጉዤ ነው። የፓምፍሌት ደካማ ዕውቀት ከቅራሪ የቀጠነ... እዚህ ነው በጣቶቼ ጠቅሼ የጠባሁት፡፡ ከአስተማርናችሁ አትጨምሩ አትቀንሱ’ የተባልነው። ወረቀት ቀይ ቀብቼ ለላብአደሩ የጮህኩ እዚህች ቤት መከዳ ላይ ነው" (ይመ ያመ ፥ 118)

አለሙ 16 ዓመቱ ቢሆንም እዛው መንገዱ ጠርዝ ላይ ባለች የጥናት ክበብ ውስጥ ተሳታፊ ነበር ። ቅራሪ ቢሆንም የማርክስን ‘ወንጌል’ ጠጥቷል ፤ ተሰብኳል። የተሰበከውን ርዕዮት አለም እውን ለማድረግ ወንጌል ነውና ፣ ርዕዮት ዓለም ነውና ራሱን በለየለት የፋንታሲ ዓለሙ ውስጥ ያገኛል ፣ እውነታ ብሎ ያለመዉን ለማግኘት ይደክማል ግን ይህቺ ርዕዮተ ዓለማዊ እውነታ ጉም ሆና ትተናለች ።

ስሎቮን ዢዤክ “Ideological fantasy structures reality. Reality is a fantasy construction, which enable us to mask the real of our desire” (The sublime object of Ideology ፥ 45)

ከላይ የተዋስኩት ሃሳብ እንደሚያስረዳው በርዕዮተ ዓለማዊ ፋንታሲ ውስጥ ነው እውነታ የሚገነባው ። ይህም የሚደረገው የመሻታችንን (Desire) እውነታን ለመደበቅ ስለሚያስችል ነው ።

በመሆኑም አለሙ በርዕዮተ ዓለማዊ ፋንታሲ ውስጥ ሚፈልገው የመሻቱ አውነታ ግን የሚጨበጥ ጉዳይ አይደለም (Ideology is the sublime object) ማርክሲዝምን ተረድቶ ሃገራዊ እሳቤ እንዲኖረው ማድረግ ፣ ማህበረሰባዊ ትርጓሜ እንዲኖረው ማስቻል የተገባ ነበር ። ሌላኛው መረሳት የሌለበት ጉዳይ ግን በተቃራኒ የቆመ ከሚመስለው ካፒታሊዝም ጋር ተመሳሳይ የንድፈ ሃሳብ መታገጊያ ማዕቀፍ (Theoretical frame work) በሄግል ዲያሌክቲክ ውስጥ የሚታይ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በዘመኑ የነበሩት የማርክሲስት እንቅስቃሴ መሪዎች የተለያዩ የጥናት ክበቦችን አቋቁመው የነበረ ቢሆንም ወደ ‘ትክክለኛው’ እርምጃ ለመምራት በትክክለኛ በጽንሰ-ሐሳብ የዳበረ የእውቀት አቅም አልነበረም ቢባል ስህተት አይመስለኝም፡፡

በወቅቱ የነበረው ሁኔታ በዋናነት ለአብዮታዊ ድርጊት እንጂ ነገሩን በአግባቡ የመረዳትና በእውቀት ስልተ ምርት ዉስጥ የመበየን አልነበረም ። በውጤቱም ከለካነው ሰነ ልቦናዊ ህመምን ፣ ማህበረሰባዊ ምስቅልቅሎሽና እና የቂም ፖለቲካን ሆነው እናገኛቸዋለን ፤ ግራ የተጋባ ትውልድ ፣ መዋቅራዊ ድህነትና ጎስቋላ ህይወት የአብዮቱ ውርሶች ናቸሁ ቢባል ስህተት አይሆንም።

ሌላው መታየት ያለበት የትምህርት እና የትውልዱ ጉዳይ ነው ። መጀመሪያውኑ ሃገሩ ማመፅ የጀመረው የራሱ እሴትና እውቀት ላይ ነው ፤ አይረቡም ብሎ ከውጭ ዘመናዊ የተባለውን ትምህርት ያውም አውሮፓውያኑ ለቅኝ ግዛቶቻቸው የቀረፁት የትምህርት ካሪኩለም ነበር።

የአብዮቱ ዘመን ትምህርት ደግሞ ይብሱን በነውጥ የታጀበ ነበር ። እስቲ ማሳያ እንውሰድ ፣
“... ትምህርት ከድል በኋላ ብዬ ሱቅ ጀርባ ወረቀት እያተምኩ የብርሐን ቀን ጠብቄያለሁ፤ ወንድ ስለሆንኩ እጆቼን ነበልባል ውስጥ ጨመርኩ ። ታዲያ ብርሃን ሳይሆን አንጀቴ ውስጥ ጠማማ ቁስል ቀረ" (ይወሰዳል መንገድ ያመጣል መንገድ.፥ 137)

አለሙ ይሆንን ነግሮን ሲያበቃ ፣ ውስብስቧ ተባረኪ የእኔንም አውነት ስሙ ትለናለች ፣

“ . ...የ ስራ ገላዬን በጨርቅ ሰወርኩ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሱሪ ለበስኩ ። በወገቤና በቂጤ መሃል ልዩነት እስኪጠፋ አሰፋሁት ። ፀጉሬን አሳጠርኩ ። በዚህ መጀመሪያ ያኮረፈኝ ዓላዛር ነው ። መማሬ ደበረኝ ።" ከትግል በሁዋላ ትምህርት እያልኩ አራት ኪሎ ሚኒሊክ ነጭናጫው ሸገኔ ጋ መመላለስ መልከስከስ አስጠላኝ (መረቅ፥ 237)

እነዚህ ግላዊ ወይም የተናጠል የሚመስሉ ትምህርት ጠልነት የወል እንደሆነ ለማሳየት ከእቴሜቴ ሎሚሽታ ለድልህ ከተኘው ስቶሪ ውስጥ ተከታዬን ሃሳብ እንውሰድ ፣

“ .... እወዲያ የኢትዮጵያ ስብስብ ፅሑፎች ያለበት ቦታ ተደፍቶ የሚያጠና የተማሪ መአት። ያው እነ ዳዊት ‘ትምህርት አቁመን እንሂድ’ እስኪሉት። እምቢ ካለም ‘ሳቦ’ ብለው አዋክበው ወደ መጣበት እናቱ ጉያ በሴራቸው እስኪከቱት። እንደ ልጅ እስኪያደርጉት። ኢንሳይክሎፔድያዎች። ሌሎች ሬፈረንስ ማቴርያልሽ‘ ያሉባቸው መደርደሪያዎች መሃል ዳዊትን ከጀርባው አየችው ተደፍቶ ሌኒንን ሲመጥ" (እቴሜቴ ሎሚ ሽታ ፥101)

ታሪኩን ልብ ብለን ካየነውና የነበረውን ድባብ በአግባቡ ከተረዳነው የአብዛኛው ተማሪ ልቦና በሌሎች የሚዘወርና ለነበረው ርዕዮተ ዓለማዊ እሳቤ መስዕዋት ለመሆን የተዘጋጀ እንደነበር እንረዳለን ፤ ሪቮ (እነ ዳዊት) የተባሉ ተማሪዎች በቀየሱለት ቦይ ለመፍሰስ የማያመነታ መሆኑ ግልፅ ነው ።

በእነዚህ ሶስት የተለያዩ ስራዎቹ የትምህርትና የትውልዱን ትስስር በተናጠል ብሎም በቡድን የነበረዉን ሁኔታ ደጋግሞ የሚነግረን ለምንድን ነው? የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ነው ።

አዳም ደራሲ ነው። ሃገሩ በትክክል ምንድን ነው ስብራቱ? የሚለውን ደግሞ ደጋግሞ እየተፈተሸ ህመሙን ያሳየናል ፤ መድሃኒቱን ይቀምማል ። የዚህም ስብራት ሁለንተናዊነት ለማሳየት ነው ልፋቱ ። የስብራታችን መጀመሪያ ዘመናዊ የተባለው ትምህርት ነው ቢባል ስህተት አይሆንም ፤ ይህም የራስ እውቀት ነፃነትን አሳጥቶናል (lack of Epistemc autonomy) ወጣቶችን በአማላይ ርዕዮተ አለም ጠልፎ ለአንድ ለታቀደ አላማ ራሳቸውን ለመስዕዋትነት እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል። ወዲህ ደግሞ ለምን ብሎ መጠየቅ የሚያስችል እውቀት ሲጠፋ ደግሞ ነገሩ ይብሳል ። መረቅ ውስጥ ያለውን ሁሌም የሚገርመኝን ሃሳብ ላምጣ ፤

" ... ወሲብ ትልቅ ጉልበት ነው፡፡ የወሲብን ስልጣን ወጣቶች ልብ ውስጥ እንይወጣ አድርገህ አምቀህ ለጫጫታ ትጠቀምበታለህ ። በየአቅጣጫው ታፍነውና አንድ የፖለቲካ መውጫ ብቻ ቀዳዳ ካበጀህለት ባሪያ አገኘህ ማለት ነው፡፡" (መረቅ፥162)

ይሄ ሃሳብ ብቻውን ወደ ብዙ የእውቀት መስመር ውስጥ ይከተናል ፤ ብዙ ወርቃ ወርቅ ሃሳብ ይወጣዋል ። ስልጣኔም ሆነ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ይህንን እምቅ ተፈጥሯዊ የወሲብ አቅምን ለራስ አላማ በማዋል ነው ታሪካዊ ቀጣይነቱ የሚረጋገጠዉ ፤ ለዚህ የፍሮድን የስልጣኔ(Civilization pathology) ዝርዝርን ማየት በቂ ነው ።

ለእኔ ጉዳይ ግን ወጣቶች በወል ርዕዮተ ዓለም ተመርተው የወል እርካታን ለማግኘት የሚዳከሩበት ጉዳይ በዢዤክ አባባል (Collective jouissance) ውስጥ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ምናልባት እዚህ ጋር "jouissance " የሚለው ቃል ፈረንሳይኛ ሲሆን ቀጥተኛ የሆነ እንግሊዝኛ ፍቺ ባይኖረውም " enjoyment " በሚለው ቃል ተተክቶ በአውድ ውስጥ ይነበባል።

ዢዤክ ይህን ሃሳቡ ሲያብራራ ፣ ብሔርተኝት ፣ ፋሺዝም ፣ ናዚዝምና ሌሎችም ርዕዮተ አለማዊ ትግሎች በዚህ በ Collective jouissance ውስጥ የሚካተቱ ናቸው ይላል ። ይህም ምናልባት ብሔርተኛነትን (nationalism) እስከዛሬ ከምናውቀው በተለየ መንገድ የሚያሳየን እሳቤ ነው።

ሌላው በጣም የደነቀኝና የገረመኝ የሶሻሊዝም የተቃርኖን ንድፈ ሃሳብ ነው። ይህም በዓለም አቀፍ ወዛደራዊነት ተንትኖና አብራርቶ ሲያበቃ ስለ ብሔርተኝነት የሚነሳው ሃሳብ ነው። ይህም አንዱ ድንበርተኝነትን ሲሽር ፣ አንዱ ደግሞ ዘውጌነትን የሙጥኝ ማለቱ ነው።

በተቃርኖ ፅንስ ሃሳቦች የተዋቀረው ሶሻሊዝም አለም አቀፋዊ እሳቤው ጠፍቶ ፣ ኢትዮጵያን ከፉ ውርሷ በሆነው ብሔርተኝነት ቅርቃር ውስጥ ይኸው መከራዋን ትበላለች።

አለሙ እንዲህ ይለናል ፣

" .... ኢንተርናሲዮናል በጉርምስናዬ ዘምሬ ፣ ስለ ዓለም አንድ መሆን ሰብኬ ብዙ ሳልቆይ የተመረረ መንደረኛ የሆንኩት እዚህ ነው .... “ (ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ ፥ 137)

ይህንን ብዙ ብዙ የሚያስብል ሃሳብ በሌላኛውን ድንቅ አሳቢ የሰሎሞን ደሬሳ ግጥም እናጠናክረው በዚያዉም መዝጊያ ብናደርገው ምን ይለናል?

ሾሾቱ ፥ ከማጠንጠ
ማርክስ ሲሉን
ዳፍንት ተጎናፅፈን
ሌኒን ሲሉን
ቦሃቃ እግር ስመን
(ውስጥ እግር ተገርፈን)
ስታሊን ሲሉን
እርጉዝ አስወርደን ህፃናት አሳርደን
ማዎ ኢልሱንግ ሲሉን
(በቱታ ጥብቆ ከስለን አይበቃ እንዳላረርን)
መንበርከክ ከጉልበት አላምደን
ከያቅጣጫ በተተፋ ፥ ትፋቱን ወርቅ ነክረን
ሾለቆ ፥ ተራራ ፥ እምነትን አሳ ‘ ደን
ማንን ልንመስል ጐፈሬ ተተኩሰን…

(ዘበት እልፊቱ ወለሎታት ፥ 5o -51)